የፕላንና ልማት ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዝያ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ቁጥር	ርእስ/ንኡስ ርእስ	ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	3
1.1.	የጥናቱ ዳራ (Backgraound Of The Study)	3
1.2.	የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ	4
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	6
1.4.	የጥናቱ ወሰን	6
1.5.	የጥናቱ አስፈላጊነት	6
1.6.	መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች	7
ክፍል ሁለት	የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና ትንተና ዘዴ	8
2.1.	የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)	8
2.2.	የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)	8
2.3.	መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)	8
2.4.	የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ	10
ክፍል ሶሥት	የሙስና ስጋት ትንተና	12
3.1.	የተቋማት አደረጃጀት	12
3.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	15
3.3.	የተቋማት ግልጽነት	17
3.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	19
3.5.	የተቋማት ንብረት አስተዳደር	20
3.6.	የግዥ አስተዳደር	22
3.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	24
3.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	26
3.9.	ኦዲትና ቁጥጥር	26
3.10.	የሙስና ስጋት	28
ክፍል አራት	መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	29
4.1.	መደምደሚያ	29
4.2.	የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	30

ክፍል አንድ
መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ እድገት እና የሰብአዊ መብት መከበር በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ፤ከህብረተሰቡ የተሰጠ አደራን ለግል ጥቅም በማዋል የሀገርን እድገት የሚያቀጭጭ፤ ሐቀኝነትን የማጉደል ወይም ሕገወጥ ባህሪ ማለት ነው፡፡ ይህም የህግ የበላይነትን እና ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን ተቋማዊ መሰረት በማቀጨጭ ለሀገር እድገት እንቅፋት ይሆናል፤ ለማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማነቆ ይሆናል፣ በመሰረተ ልማት፣ በተቋማት እና በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማዳከም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምህዳርን ያጎለብታል፣ የሞራል እሴቶች ማሽቆልቆልን ያመጣል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና የግሉ ዘርፍ ተቋማት ጥረታቸውን እንዲሁም ሀብታቸውን ስትራቴጂካል በሆኑ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ የተለያዩ ጥናቶች በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው

እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ቢገባም እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በተለያዩ ዘርፎች ስር በሚገኙ ተቋማት ሊከሰቱ ለሚችሉ የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአሰራር ሥርዓት፣ የግለሰቦች የሥነ-ምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የቁጥጥር ሥርዓት መላላት፣ የጥቆማ አቀራርብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር እና የመረጃ አያያዝ ደካማነት እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መቃኘት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ስጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ በፕላንና ልማት ዘርፍ ስር በሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1.2. የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

ፕላንና ልማት ሚ/ር የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት እንደገና የተደራጀ አስፈጻሚ ተቋም ነው፡፡ በዘርፉ ስር ያሉ አራት ተቋማት ጠቅላላ የሰው ሀይል 3,080 ነው፡፡

ዘርፉ የልማት፣ የሀገራዊ የስታትስቲክስ፣ የሥነ-ሕዝብ፣ የአየር ንብረት ለውጥንና አካባቢን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፤ ሀገራዊ የረጅም ዘመን አመላካች የልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ በዚህም ላይ ተመስርቶ የሀገሪቱን የአጭርና የመካከለኛ ዘመን የልማት ፕላንና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ትንበያና የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፉ የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት እና

የወጪና የገቢ ንግድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሎችንና የዜጎችን ፍትሐዊ የመልማትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ የኢኮኖሚና የልማት ፖሊሲ ትንተናና ጥናቶች ያካሄዳል፤ ስትራቴጂካዊ የሶሺዮ ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ይለያል፤ በትንተናና ጥናቶች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የፖሊሲ ምክረ- ሀሳቦችን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል በተለያዩ አካላት የሚመነጩ የልማት ፖሊሲዎችን የተጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፡፡

በዘርፉ ስር ያሉት ተቋማት የየራሳቸው ልዩ ባህሪ ስለሚኖራቸው ከዚህ በታች የተጠቀሰው የሚ/ር መ/ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ ነው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ፡- ኢትዮጵያን የብልጽግና ተምሳሌት ማድረግ፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ

- ለአገሪቱ ዘርፍ ብዙ የልማት መስኮች የፖሊሲ ትንታኔዎችን፣ አመራርና ድጋፍ መስጠት፣
- የዘርፍ መ/ቤቶችንና የመንግስት ተቋማትን በማቀናጀት የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት እቅዶችን ማዘጋጀት፣
- ለልማት ፖሊሲ፣ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች መረጣ፣ ግምገማ እንዲሁም ቅደም ተከተል እንዲረዳ የመንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደር እና አመራር አቅም ማጎልበቻዎችን ማበልጸግ፣
- ለልማት እቅዶች ፖሊሲና ፕሮግራሞች ላይ ወቅቱን ጠብቆ ቁጥጥር እና ግምገማ ማድረግ፣
- ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት እና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ ግምገማዎችን ከዘርፎች ትንታኔ ጋር ያጠቃለለ መደበኛ አካውንት ማዘጋጀት

በዘርፉ ውስጥ ባለ ተቋማት ዋና ዋና አላማዎች፡-

- ሁሉም አገራዊ የልማት ዕቅዶች በአግባቡ የታለመላቸውን ግብ መምታታቸውን ማረጋገጥ ነው፤

- በቆጠራ፣በናሙና ጥናት፣በማያቋርጥ ምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት የተሰበሰቡ የኢኮኖሚያዊ፣የማህበራዊ እና የስነ-ህዝብ፣የስታስቲክስ መረጃዎችን በተቀናጀ አሰራር ሰብስቦ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ነው፤
- በሀገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ የተመለከቱ መሰረታዊ መርሆች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፤
- ጥናትነ ምርምር ማካሄድ፣የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሰቦችን ማመንጨት እና የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶችን ማዘጋጀት ነው፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ግምገማዊ ጥናት ዋና ዓላማ በፕላንና ልማት ዘርፍ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

ንዑስ አላማዎች፡-

በፕላንና ልማት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት

- የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ከህዳር/06/2015ዓም እስከ ሚያዚያ/30/2015ዓም የኢፌዴሪ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር እና በስሩ ባሉ አራት ተጠሪ ተቋማት ላይ አደረጃጀት፤ ተቋማዊ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር የግዥ አስተዳደር፣የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና ኦዲትና ቁጥጥር የአሰራር መርሆችን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት በዘርፉ ባሉ ሁሉም ተቋማት የፕሮጀክት ስራዎች ስለመኖራቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ሪፖርት ውስጥ ፕሮጀክት አስተዳደር ትንተና አልተካታተም፡፡

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በአሰራር እና የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችና ብልሽቶች በመለየት የሙስና ቅደመ መከላከል እድል ስራዎች ለመተግበር የሚግዝ መሳሪያ ነው። ዋናው የግምገማዊ ጥናቱ አላማም የሙስና ስጋቶች በተጨባጭ መረጃ በተደገፈ በመለየት የመከላከል ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ማስቻል ነው። እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የአደጋ ለውጦችን ለመከታተል ለፀረ-ሙስና ትግል ሥራ እንደ መነሻ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል። በዚህ መሻነት ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ የሚታዩ የሙሰና ስጋቶች በአስራ አንድ የትኩረት ጉዳዮች ለመየት የተካሔደ ነው። ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ፋይዳው በፕላንና ልማት ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማ የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን በመለየት፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ በማመንጨት የሙስና መከላከል ስልት ማመላከት እና በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

1.6. መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ ሲካሄድ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ችግሮች አጋጥመዋል።

- የተቋማት ሰራተኞች በተያዘላቸው ቀጠሮ ያለመገኘትና ጥናቱን የሚያከናውኑትን ባለሞያዎች የማመላለስ፣
- የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣
- በተቋማት የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ችግር መኖር፣
- የሥልክ፣ የትራንስፖርት፣ የሰው ሀይል እና የጊዜ እጥረት፣

ክፍል ሁለት

የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና ትንተና ዘዴ

2.1. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር የፕላንና ልማት ዘርፍ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ በአብዛኛው ዓይነታዊ እና በተወሰነ ደረጃ የአሃዛዊ (mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በማጣመር በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆነው መረጃም ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የመሰብብ ስራ ተሰርቷል፡፡

2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)

ይህ ጥናት በዋነኝነት የየፕላንና ልማት ዘርፍ በሚገኙ ~~አምስት (5)~~ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የአይሲቲ የጥናት መረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

2.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

2.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ

በዚህ በዘርፍ ሥር በተደራጁት ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 11 የትኩረት ርእሰ ጉዳዮችን የመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመረጃ መሰብሰቢ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጠይቅ ዙርያ ላይ ለመረጃ ሰበሳቢዎች ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ

መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ በመፍጠር መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብኣት የሚሆነው መረጃ የተሰበሰበባቸው የትኩረት ርዕስ ጉዳዮችም ዝርዝር በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ቀርቧል፡፡

2.3.2. የሙስና ሥጋት መንስኤዎችንና አመላካቾችን ልየታ

የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ሊያሳዩ የሚችሉ አመላካች ርዕሰ ጉዳዮች መለየት ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነትም አስራ አንድ ተለየይተው የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቁ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት የትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመከናወኑ ወይም ሲከናወን የተስተዋሉ ችግሮችን ከሙስና እና ብልሹ አሠራር አንፃር በመቃኘት የሙስና የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካች መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያው መጠይቅ ውስጥ የተካተቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሰ ጎዳዮች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ተቋማዊ አደረጃጀት፡-** ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አስራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተልዕኳቸውን የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የህግ ጥሰቶችን በህግ ስርዓት በማስተካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ግልፅነት፡-** የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙበት ዋና አላማ ለህዝብ አገልግሎት መስጠት እስከሆነ ድረስ ተግባር፣ሃላፊነታቸውና የአሰራር ስርዓታቸውን ለተገልግጋዩ ማህበረሰብ ግልፅና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት አገልሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተደራሽነት መርሆች ምን እደሚመስሉ የሚፈተሸበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ፡-** ሙስና እና ብልሹ አሰረሰርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣አፈፃፀምንን ለማሻሻል ተቋማት የአሰራር መመሪያ፣ አዋጅና ደንብ ያወጣሉእንዲሁም በየ ጊዜው ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት ቁመና ምን እንደምሚስልና የሚያወጧቸው የአሰራር መመሪያዎች ምን ያክል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስለመናቸው የምንፈትሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር፡-** የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ አገልግሎት የማይሰጡ፣ መወገድና መጠበቅ ያለባቸው የተቋማት ንብረቶች የተያዙበት ስርዓት ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሸበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የግዥ አስተዳደር፡** ግዥ በእቅድ፣በመመሪያና በቴክኖሎጅ በታገዘ መልኩ በመፈፀም ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉበትን ስረዓትና አሰራር የመፈተሸበት የጥኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሰው ሃብት አስተዳደር፡** አቅምና ብቃት ያለው የሰውሃበት መረጃ አያያዝን እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የሚያስተዳድሩብትን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሀብት ምዝገባ፡ ሀብት** ምዝገባ አንዱ የግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርህ ስለሆነ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብታቸውን ስለማስመዝገባቸው የምንፈሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ፕሮጀክት አስተዳደር፡** ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ፕሮጀክቶች የሚያስተዳድሩበትና የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ብክነትን በቀነሰ እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመሆኑ የምንገመግምበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የኦዲት ቁጥጥር፡** የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚገመገሙበት፣ ውይይት የሚደረግበት እንዲሁም የማስተካያ አስራሩ ምን እንደሚመስል ተቋማት የሚገመገምበት የትኩረት መስክ ነው
- **የተቋማትን ልዩ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ልየታ፡** ተቋማት የጋራ ከሚያደርጓቸው የድጋፍ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የተቋቋሙት ልዩ ተልዕኮ ያላቸውን የተጋላጭነት ሁኔታ የተለየ የሚያደርገው በመሆኑ ልዩ የሆኑት የሚታዩበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

2.4. የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ

የተሰበሰበው መረጃ ከመተንተቱ በፊት ከየተቋማቱ መረጃዎች በርእሰ ጉዳች ከተለዩ በኂላ የማደራጃት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተደራጀው የሰነድ መረጃ ለማውጣት (extract) እንዲቻል በየዘርፉ የጥናት ቡድኖች ተዘጋጅተው ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ መረጃው በማውታት ሂደትም በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ ተቋማቱ ማከናወን ሲገባቸው ያለከናወኑት ተግባር፣

ተግባራቱን ሲያከናወኑ የተስተዋሉ ችግሮችንና ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም በተግባራት ክንውን ወቅት የተስተዋሉ ለሙሰና የተጋለጡና ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አስችሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ከአሉት ዓይነታዊ መረጃ አተናተኖች ውስጥ ጭብጥ ተኮር (Thematic Analysis) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ሪፖርት አቀራረብም አይነታዊ ገለፃ ዘዴ (Descriptive Method) ተግባራዊ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትንተናው ሂደትም መረጃዎች በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳረቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ይህም ድምዳሜ ላይ ከመድረሳችን በፊት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ክፍል ሦስት
ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ትንተና

የፕላንና ልማት ዘርፍ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በአስራ አንድ ጭብጦች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

3.1. የተቋማት አደረጃጀት

በፕላንና ልማት ዘርፍ ስር ከሚገኙት አራት ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸውን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት አቋቁመዋል፡፡ ከተፈቀደው መደብ አንጻር 85 በመቶ የሚሆኑት የዘርፉ የስራ መደቦች በሰው ሃይል መሟላቱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በጀትን በሚመለከት በሁሉም ተቋማት ያሉት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ፕሮፖዛል አዘጋጅተው በሚጠይቁበት ወቅት የሚፈቀድበት አሰራር (ፑል ሲስተም) እየተተገበረ እንደሆነ ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ውስጥ ያሉት በአራቱም ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ እንዳላቸው የሚገልፅ መረጃ ተመላክቷል፡፡ ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር፣ ሁሉም በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን የተሟሉ መሆኑን በተደረገው ምልከታ ተረጋግጧል፡፡ የተወሰኑ ተቋማት (የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) መከታተያ ክፍሎች መደራጀታቸውን እንጂ ሥራቸውን ሊያሰሩ በሚያስችል መልኩ ከኃላፊዎች የቁሳቁስና ምቹ የሥራ አካባቢ ከመፍጠር ድጋፍና ትብብር እንደማይደረግላቸው በተደረገው ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ከሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የሀብት ብክነትንና ብልሹ ሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዥ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ፣ በቢሮ እና በሰው ኃይል የተሟላ መሆኑን በምልከታ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ግን በሚ/ር መ/ቤቱ ውስጥ የህግ ጉዳዮችን ሥራ ሊሰራ የሚችል ባለሙያ በክፍሉ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተቋሙ ብልሹ አሰራሮች እንዳይከሰቱ እና በህግና በእውቀት ላይ ተመስርቶ ሊፈፀሙ የሚችሉ የተለያዩ ውሎች እና ተዛማች ስራዎችን

የሚሰራ ራሱን የቻለ የህግ ባለሙያ አለመኖሩ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡

በዘርፉ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተተገበሩ በአብዛኞቹ የዘርፉ ተቋማት ቢሆንም አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ግን ሁሉም የጥቆማ መቀበያዎች ተግባራዊ እየተደረጉ አለመሆኑ በምልከታ ታውቋል፡፡ በጥቆማ የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ ተግባራትን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የጥቆማ አቀባበል ስርአት አለመዘርጋት እና ተደራሽ አለማድረግ በዘርፉ ውስጥ ለሙስና ተጋላጭነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

በፕላንና ልማት ዘርፍ ስር ከሚገኙት ተቋማት የተወሰኑ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሌሎች የሥራ ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በተወሰነ ደረጃ በቅንጅት እንደሚሰሩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ በቅንጅት ለመስራት የሚያስችላቸው ህጋዊ የሆነ የስምምነት ሰነድ ግን የላቸውም፡፡ የህግ ባለሙያ ከሌለው ከሚ/ር መ/ቤቱ ውጭ ባሉት 3 ተቋማት ውስጥ ውጫዊ እና ውስጣዊ ውሎች ላይ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ እንደሚያደርግ እንዲሁም ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት እንዳለ ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር በሚ/ር መ/ቤቱ ግን ይህ አሰራር አለመኖሩ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሚ/ር መ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት መኖሩን የሚያሳይ መረጃ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ከሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ጉዳዮችን በሚመለከት ለስነ-ምግባር ባለሙያዎች የተጠየቀ ስልጠና ላይ በጉዳዩ ያልተጋበዙትን የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት እንዲሳተፉ ተልከው እንደነበር የታወቀ ሲሆን፣ በዳይሬክተሮች እና በጽህፈት ቤት ኃላፊዎች መካከል ጣልቃ ገብነት እንደሚታይ መረጃዎች ያሣያሉ፡፡ ይህ ዓይነት ጣልቃ ገብነቶች በተቋማት መኖር አገልግሎት አሰጣጡን ከማንተት አልፎ ለጥቅም ግጭት ሊያጋልጥ ስለሚችል በትኩረት ሊሰራበት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተልዕኮና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል በተለይ በሰው ሃይልና በጀት ጥሩ ቁመና ላይ የማይገኙ በመሆናቸው ለሥነ-ምግባር ጥሰቶችና እና የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ የስነምግባር ክፍል በሚፈለገው ደረጃ የሰው ሃይል አለሞሟላት የሚያመላከተው ዋናው ጉዳይ ሙስናንና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት የሚደረገው ጥረት ላይ እክል ሊፈጥር መቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም ተቋማት ስነምግባር ክፈሉ በማደራጀት በኩል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ክፈተት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ በጅት በፑል መሆኑ የስነ ምግባር ክፍሉ በነፃነት ስራው በአግባቡ እንዳይሰራ ሊያደርገው መቻሉ ሳያንስ ለአመራሩ ጣልቃ ግብነት ሊጋልጠው ይችላል፡፡ ክፍሉ በጀት መጠቀም የሚችለው አመራሩ ሲፈቅድ ብቻ በመሆኑ ስራዎች በአመራሩ በጎፍቃድ ላይ የተመሰረቱ ሊሆሁ የሚችሉበት እድል ሰፊ ይሆናል፡፡ ውጤቱም የመንግስት ስራ በአግባቡ ያለመምራት ችግር ለመኖሩ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡
- ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አጋዥ ከሆኑት የስራ ዘርፎች መካከል የህግ አገልገሎት ክፍል አስተዋፅኦና ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በዘርፉ በሚገኙ የተወሰኑ ተቋማት የህግ ክፍሉን በሚፈለገው ደረጃ የማደራጀት ስራ አለመከወናቸው ታይቷል፡፡ ስለሆነም በሚፈለገው ደረጃ በሰው ሃይል የተደራጀ ክፍል አለመኖር ተገቢው ህግነክ ምክር ለተለያዩ የስራ ክፍሎች መስጠት ስለማይቻል ተቋማቱን ለህግ ጥሰት ሊያድረጋቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ በዘርፉ ስር ባለ አንድ ተቋም የህግ ባለሙያ እያለ የህግና የውሎች አስተያየት የሚሰትበት ልም አለመኖር ውሎች ለህግ ጥሰት ሊጋለጡ እንደሚችሉ ማሳያ ነው፡፡ ስራውን የህግ ክፍል መኖር ተጠያቂነት ለማስፍን ካለው አስተዋፅኦ በተጨማሪ የቅድመ መከላከል ስራ ለመስራት የሚኖረው ሚና የጎላ ነው፡፡
- ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከ መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም የጋራ ትንተና ለማካሄድ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው፡፡ ይህም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ሙስናን ለመዋጋት የሚደረገው ጥረት ውጤታማነት ላይ

አሉታዊ ሚና ሊኖረው ይችላል፡፡ ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማደረግ ካልተቻለም ሰራተኞች ለመሳተፍ የሚስችላቸውን መድረክ ስለሚጡ ሙስናን ለመዋጋት የሚደርጉት ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

3.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

ተጠያቂነት ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት ጋር በተያያዘ አፈፃፀሙን በመገምገም ለሚፈጠሩ ጉድለቶች እና ጥፋቶች በኃላፊነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በተለይ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ መንግስታዊ ተቋማት የሚያስተዳርሩትን የህዝብ ሀብት በተገቢው መንገድ ለህዝብ አገልግሎት የማዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ የህዝብ ሀብት እንዳይባክንና የመንግስት ስልጣን አላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል የማረጋገጥ ስራ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር ተያያዥ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡ በፕላንና ልማት ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት ላይ የሙስና ስጋት ጥናት ባይጠናም የሙስና መከላከል የአሰራር ስርዓት ጥናት ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በስተቀር ሌሎቹ 3ቱ ተቋማት እያጠኑ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሁሉም የዘርፉ ተቋማት የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል የሚጠና መሆኑ የሚያሳይ የቀረበ መረጃ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከደንበኞች ለሚነሱ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥ ስራ አለመስራት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ የሚችልበት እድል ሰፊ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር በዘርፉ ስር የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀታቸውን ከሰነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በተቋማት የተዘጋጀው መመሪያ በሚመለከት የቆየ ሰነድ መሆንኑ ለማየት ተችሏል፡፡ የሥነ-ምግባር ደንቡ ለሰራተኞች ተደራሽ መሆኑንና ስልጠና የተሰጠ ስለመሆኑ የቀረበ መረጃ የለም፡፡

በዘርፉ በሁለት ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የቀረበ ቅድመ መከላከል ስራዎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮችና ተግባራት ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል የጥቆማ ሥርዓት ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን ከቀረቡ ማስረጃዎች ለማየት ተችሏል፡፡ ለአብነት ያህል በ2014 በሚ/ር መ/ቤቱ ከነዳጅ አጠቃቀምና የመኪና ስምሪት በተመለከተ ከመ/ቤት ውጭ ሲያድሩ ብሎኬት መጫኛ እና ሙሽራ ማጀቢያ በማድረግ የተቋሙ ሀብት ሲባክን የነበረውን የቀረበ ጥቆማ መሰረት በማድረግ በተወሰደ ማሻሻያ እርምጃ እና የውሳኔ ምክረ ሃሳብ የቀረበበት ጉዳይ ከሰነድ ምልከታ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሆነው በፕላንና ልማት ሚ/ር በስነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት የቀረቡ ክሶች ሁለት ፈጻሚዎች ላይ ሲሆን፣ 100% ውሳኔ የተሰጠ መሆኑ ከተሰበሰቡ የሰነድ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በሁለት ተቋማት ባለፉት ሁለት ዓመታት 24 ቅሬታዎች ቀርበው 100% ውሳኔ በማስተላለፍ ቅሬታዎችን መፍታት እንደተቻለ ከሰነዶች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍሎችን የስራ ክንውን ሪፖርት በተቋማቱ የበላይ አመራሮች ተከታታይነት ያለው ክትትልና ግምገማ እንደማይደረግባቸው በጥናት ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ የስራ አፈጻጸም ግምገማ እንደማንኛውም የስራ ክፍል አጠቃላይ ግምገማ ሲካሄድ አብሮ እንደሚገመገም ከተሰበሰቡ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- ተቋማት በአሰራራቸው ላይ የሙስና ስጋትን ለመቀነስ ከሚጠበቅባቸው ተልዕኮ አንዱ ጥናቶችን ማካሄድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ውስን ጥናቶች የተካሔዱበት ሁኔታ ቢኖርም የችግሩ ስፋትና ጥልቀት በሚመጥን መልኩ አለመካሄዳቸው ጥናቶቹ ውስንነት ያለባቸው መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ ጥልቅ ጥናት አለማከሄዱ ከልምድ ውስንነት ሊመነጭ የሚችል ቢሆንም ችግሮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ መፍትሄ የመፈለግና የመስጠት

ተቋማዊ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት አነስተኛ መሆን አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡ የተገልጋዮች ችግር በተጠና መንገድ ለይቶ እርምጃ መውሰድ ባህል አለመዳበሩም ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ውስንነት ያለው መሆኑ ያሳያል፡፡ ተገልጋዮች ተኮር ጥናት አለመካሄድም ተቋማት ማህበራዊ ተጠያቂነት ለማስፈን የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተቋማት ጥናት የማካሄድ ልምድ አለማዳበራቸው ኃላፊነታቸው በመወጣት ረገድ ሰፊ ክፍተት እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት ኃላፊዎች በአሰራር ሥርዓት ጥናት የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦችን ተግባራዊ እንዲሆኑ በባለቤትነት ትኩረት ሰጥተው ክትትል ስለማያደርጉ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች እንዲበራከቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

- አንዳንድ ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጁ መሆኑን በመልካም የሚወሰድ ልምድ ቢሆንም ከተግበራዊነቱ አንፃር ሲታይ አመርቂ ደረጃ ነው ብለን መውሰድ አንችልም፡፡ ይሁንእንጂ የተዘጋጁት ሰነዶች ከወቅታዊነት አኳያ ውስንነት እንደሚስተዋልባቸው እና በአስፈፃሚው በኩል ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን መመልከት ተችሏል፡፡ በመሆኑ ደንቡ በአዲስ መልክ ሊሻሻል እና ለሰራተኞቻቸው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ከተቋመት ይጠበቃል፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ተገባራዊ ተደርጎ ተጠያቂ የሆኑ ክፍሎች ወይም ሰራተኞች ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ድንቡ ተጠያቂነት ለማስፈን አለመቻሉ አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ተቋማት የስነምግባሩ ደንቦች የማሻሻል ወይም አዲስ የማዘጋጀት ስራ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

3.3. የተቋማት ግልፅነት

ተቋማዊ ግልፅነት ማለት የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥን ያጠቃልላል፡፡ ተቋማት ሥራቸውን ለተገልጋዮቻቸውና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ አላማቸውን ለማሳካትና አፈፃፀማቸውን ለማሳደግ ሚናው የጎላ ነው፡፡ ይህን ለማሳካትም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅና አሳታፊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር እየተገባ መሆኑን ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ በማድረግ በኩል እየተሰሩ ያሉ ስራዎች መኖራቸው ቢገለፅም በአጥጋቢ መልኩ እየተተገበሩ ስለመሆናቸው አሳማኝ መረጃ ማቅረብ አልተቻለም፡፡ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚካሄድ ተሳትፎ እና ውሳኔዎችን ተደራሽ ማድረግን በሚመለከት በማኔጅመንት ደረጃ ከሚደረግ ውይይትነ ቃለ-ጉባኤ ለማየት እንደተሞከረው የተለያዩ ውሳኔዎች የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የሚሳተፉ ሲሆን ለሁሉም አካላት ተደራሽ ማድረግ የተለመደ አይደለም፡፡ አንዳንድ ውሳኔዎች በተለይም ለህዝብ ይፋ መደረግ ያለባቸው በመገናኛ ብዙኃን እና በማህበራዊ ሚዲያ በተከታታይ ተደራሽ የሚደረጉ ሲሆን፣ አንዳንዶች ግን በደብዳቤ ብቻ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ተደራሽ ይደረጋሉ፡፡ መረጃዎችን በሶሻል ሚዲያ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር በፌስቡክ ገፅ እና በቴሌግራም ቻናል መረጃዎች የማድረስ ስራም እየተሰራ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በተለይ ለጨረታ ማስታወቂያ አዲስ ዘመን ጋዜጣን የሚጠቀሙ ሲሆን መረጃ ለማሰራጨት ግን የራሳቸውን ማህበራዊ ሚዲያ በብዛት ይጠቀማሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች በየሩብ አመቱ የመገምገም ስራ አየተሰራ መሆኑን በበጎ የሚወሰድ ቢሆን ችግሮች ለይቶ እርምጃ በመውሰድ በኩል ያለው ቁርጠኝነት የሚያሳይ መረጃ ግን አልቀረበም፡፡ ይህም የሚወሰዱ ማስተካከያዎችና እርማቶች ግልፅነት የጎደላቸ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመላካች ነው፡፡ ሌላው በተቋማቱ የሚስተዋለው ክፍተት የውሳኔ ቃለ ጉባኤዎች ተደራሽ አለመሆናቸው ግልፅነትን ከማሰፈን አንፃር ውስንነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የውሳኔ ቃለጉባኤዎች ተደራሽ አለመሆናቸው አመራሩ በስልጣን አላግባብ በመገልገል ውሳኔ ሲያሳልፍ ወይም ውሳኔዎች ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችልበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ሙስናን ለመዋጋት ያለው እድል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

- ተቋማት የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ስለሚሰሯቸው ስራዎች ተደራሽ የሚያደርጉ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በተለይ በማህበራዊ ወይም ድህረ-ገፅ መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የማድረግ እየተሰራ መሆኑን ነው፡፡ ይሁንእንጂ መረጃዎች ተካታታይ በሆነ መንገድ ለባለድርሻ አካለት የማድረስ ውስንነት መኖሩን ከድህረ-ገፅ ምልከታ መረዳት ይቻልል፡፡ በድህረ-ገፅ ሚወጡ መረጃዎች ጊዜ ያለፈባቸውና በየጊዜው ማይታደሱ (not updated) መሆናቸው መመልከት ግልፅነት ለማስፈን የሚደረገው ስራ አመርቂ አለመሆኑ ያሳያል፡፡ የአንዳንዶቹ ተቋማት ድህረ-ገፅም በተግባር እየሰሩ አለመሆናቸው የኢንተርኔት ዳሰሳ ማድረግ በቂ ነው፡፡ መረጃ ግልፅ በሆነ መንገድ ለባለድርሻ አካላትና ዜጎች ተደራሽ አለመሆኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመከላከል ረገድ ያላቸው አስተዋፅኦ ውስን እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

3.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ለሙስና መከላከያ የሚያገለግሉ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ከተዘጋጁ ረጅም ጊዜ የሆናቸው የሥነ-ምግባር መመሪያዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በጥናቶች በመመስረት አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ በተቋማቱ የተሰራበት ሁኔታ መረጃ የለም፡፡ በሚወጡ ህጎችና ድነቦች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ስለጠና ስለ መሰራቱ የሚያሳዩ ሰነዳዊ መረጃ ማገኘት አልተቻለም፡፡ ፀድቀው የሚወጡ የሥነ-ምግባር መመሪያዎች (ደንቦች) ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ ረገድ በተለይም በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየሰሩ ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ የተገኘው መረጃ ሁሉም ተቋማት ከረጅም ጊዜ በፊት እንዳዘጋጁ እና በአሁኑ ጌዜ በኃላፊዎች ትኩረት ያልተሰጠው ሥራ ሲሆን፣ አንዳንድ ተቋማትም ተቆጣጣሪ እንጂ አገልግሎት ሰጪ ስላልሆንን ቻርተሩን ለመተግበር አስፈላጊ አይደለም እስከማለት እንደደረሱ በቃለ መጠይቅ ለማወቅ

ተችሏል፡፡ ሰነዱ የቆየ ቢሆንም ለተገልጋዮች ተደራሽ መደረጉን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ አልተገኘም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና የመስጠት ባህል አለመኖሩ በአፈፃፀም ላይ ክፍተት ከመፍጠሩ ባሻገር ህጎች ሲጣሱ ለማረምም ችግር መፍጠሩ አይቀርም፡፡ አስፈፃሚው አካልና ተገልጋዩ በህግ ዙርያ ያለው ዕውቀት ውስንነት የሚሰተዋልበት ከሆነ አለአግባብ ስልጣን የመገልገል ስጋቶች ሲኖሩ የቅድመ መከላከል ስራ ተግባራዊ ለማድረግ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ይታመናል፡፡
- ነባር አዋጆች መመሪያወች እና ደንቦች በየጊዜው የማሻሻል ሲራ እየተሰራ አለመሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ተጠያቂነት ለማስፈን ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ተግባራዊ መደረጋቸው ሙስናን ከመከላከል አንፃር ያመጡት ለውጥ ወይም ያሳደሩት ተፅኖ መመርመር እና ማጥናት ካልተቻለ ተጠያቂነት ለማስፈን ያላቸውን ጠቃሚነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገባቸዋል፡፡ የተፅኖ ጥናት ማካሔዱ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን በተጨባጭ መረጃ ተመስርቶ ለማሻሻልና አዳዲስ ህጎች ለማውጣት አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ ማሻሻዎች እና አዳዲስ ህጎች ለብዙ ጉድለቶች የተጋለጡ ሊሆኑ ስለሚችሉ ለመተግበር አስቸጋሪ ከመሆናቸው ባሻገር ለብልሹ አሰራርና ሙሰና መከሰት አስተዋፅኦ ሊያድርጉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የዘርፍ አመራሮች ህጎች ከማሻሻላቸው ወይም አዲስ ህግ ከማውጣታቸው በፊት አስፈላጊው የተፅኖ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ አሰራሩን ከማዘመን ባሻገር ብልሹ አሰራሮችና ሙስና ለመዋጋት ተጨባጭነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

3.5. የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ማለት የተገዙ ንብረቶች መረከብን፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅን፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርዓት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

የቀረቡት ሰነዶች እንደሚያሳዩት በሁሉም ተቋማት የሚገኙ ንብረቶችን የመጠበቅ እና በያዓመቱ የንብረት ቆጠራ ስራ እየተሰራ መሆኑን የሚያመላከቱ ናቸው፡፡ የተገዙ እቃዎች የግዥ መመሪያ ሥርዓት የተከተሉና በሠነድ እየተመዘገቡ መረጃዎች በአግባቡ እንዲደራጁ ከማድረግ አንፃር የተሰራው ስራም በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት የተደረጉት የሰነድ ፍተሻዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን የንብረት አያያዝ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥራ እንደማይሰራ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሌላው ከንብረት አያያዝ ጋር የሚጠቀሰው ጉዳይ የካይዘን ንብረት አሰተዳደር ስርዓት ሲሆን፣ ስርዓቱ በተቋማቱ ስለመተግበሩ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ከተገኘው መረጃ መገነዘብ እንደተቻለው አብዛኛው በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶችን የመለየት ስራ ይሰራል፡፡ በሚ/ር መ/ቤቱ፣ በኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት እና በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተቋማት በጠቅላላው ብዛታቸው 4,143 እና በገንዘብ 10,600,404.00 ብር የሚሆኑ ንብረቶች ተወግደዋል፡፡ የሚወገዱ ንብረቶች ከመወገዳቸው በፊት አስቀድሞ በተዘጋጀ ስቶር ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ የሚደረግላቸው መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ ንብረቶቹ የሚወገዱበት አግባብም በሽያጭ እና በስጦታ/በእርዳታ መልክ በሚመለከተው አካል ፀድቆ የማስወገድ ስራ እንደተሰራ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- በዘርፉ ያሉ ተቋመት አመታዊ የንብረት ቆጠራ ቀጣይነት ባለው የተደራጀ መንገድ እያካሄዱ አለመሆናቸው ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ቆጠራው ብክነትን ከመከላከል ባሻግር ስርቆትን ለመከላከል አጋዥ ሚና ሊኖረው እንደሚችል እሙን ነው፡፡ የንብረት አስተዳደር አሰራሩ በተገቢው ጥበቃና ቁጥጥር ካልታገዘ የመንግስት ንብረቶችን ለስርቆት፣ ለብልሽት እና ለቃጠሎ የመዳረግ ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ጥቅም ላይ ውለው ወደ ንብረት ክፍል የሚመለሱ ንብረቶችን መስራት መቻል እና አለመቻላቸው በባለሙያዎች ሳይረጋገጥ ገቢ ማድረግም ተቋምን ለሃብት ብክነት ማጋለጡ አይቀርም፡፡ ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ስራ ሊገቡ የሚችሉ ንበረቶችን አላግባብ እንዲወገዱ ወይም እንዲከማቹ የሚችሉበት አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ በተቋማት ንብረት የሚያስተዳድሩበት መንገድ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በተጠናከረ መልኩ ለመዋጋት እንዲቻል ተደርጎ መተግበር አለበት፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የዘርፉ ተቋማት ተከታታይነት ባለው መልኩ የተሟላ ንብረት ቆጠራ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
- ካይዘን ዋና ዓላመው የሀብት ብክነትን መከላከል ነው፡፡ ንብረትን በተደራጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለማስተዳደርና መቆጣጠር አሰቻይ ሁኔታ በመፍጠር ሁሉም የተቋም የስራ ክፍሎች እና ሰራተኞች ሃብትን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ያግዛል፡፡ ካይዘን አለመተግበሩ እቃዎች በክምችት እያሉና ስራ ላይ ሳይውሉ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን አላስፈላጊ ክምችትን በመፍጠር የህዝብ ሀብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በየተቋማቱ የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ በአውቶሜሽን የታገዘ አለመሆኑን ለመግንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የንብረት አስተዳደር ዘመናዊ አሰራር የተከተላ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ይህም ስርቆትና ብክነት ለመከላከል የሚያስችለውን እድል ያመክነዋል፡፡ በተቋማት የካይዘን ንብረት አሰተዳደር ስርዓት አለመተግበሩ ለንብረት ብክነት፣ ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና ስጋት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

3.6. የግዥ አስተዳደር

የዘርፉ ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብዓቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ማግኘት ይጠበቅባቸዋል። በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ግብዓቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርዓትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል።

በዘርፉ ስር ባሉ አብዛኛው ተቋማት የግዥ ስርዓትና የግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ ግዥ የሚከናወነው በእቅድ፣ ከየክፍሉ በተሰበሰበ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ስለመሆኑ ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህ ሁኔታ መተግበሩ ግልፅነትን ከማስፈኑ ባሻገር በዘፈቀደ የሚታዘዙ ግዥዎች ሊያመጡ የሚችሉትን የሙስና ስጋት ይቀንሳል።

በዘርፉ ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት ከግዥ በፊት የገበያ ጥናትን እንደማይከናወን እና የገበያ ጥናት አድራጊ ኮሚቴም እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል። የኢፌድሪ ስታትስቲክስ አገልግሎት በአገር አቀፍ ደረጃ የገበያ ጥናት ስለሚያካሂዱና ይህን የጥናት ውጤት አልፎ አልፎ ከግዥ በፊት እንደገበያ ጥናት ግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት በቃል ገልፀዋል።

በ2014 የበጀት ዓመት ሚ/ር እና በባለስልጣን መ/ቤቶች የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣

ተ.ቁ	የአፈጻጸም ማሳያዎች	በቁጥር	በገንዘብ በብር	መግለጫ
1	በዕቅድ የተገዙ	369	55,710,781.00	
2	ያለዕቅድ የተገዙ	16	650,000.00	
3	በፕሮፎርማ የተገዙ	123	5,153,587.79	
4	በውስን ጨረታ የተገዙ	1	791,500.00	
5	በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ የተገዙ		1,362,000.00	
6	ቅሬታ የቀረበባቸው ግዢዎች	-	-	
7	የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች	-	-	

በዘርፉ ባሉ ሁለት ተቋማት የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ መሰረት በፕሮፎርማ እና ያለዕቅድ የሚፈፀሙ ግዥዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ ሲሆን፣ የቀጥታ ግዥዎችና ለአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ የሚሰጡበት አጋጣሚ እንዳለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ ግዥዎች እንዲካሄዱ የሚያስገድድ ምክንያት (ህጋዊ መሰረት) ሊኖር የሚችል ቢሆንም ግዥዎቹ ለምን በግልፅ ጨረታ እንዳልተከናወኑ፣ ሳይታቀዱ እንደተገዙና፣ ከአንድ አቅራቢ እንደተገዙ ምክንያቱን የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም፡፡ በዘርፉ ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት ከIFMIS በስተቀር ዲጂታላይዝድ የግዥ ስርአትን (የግዥ ሥርዓታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል የመንግስት ኤሌክትሮኒክስ ግዥን (e-GP Electronic Government Procurement) የግዥ ስርዓት ተግባራዊ ስለመደረጉ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ይህን የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ስርአት (ዲጂታል ሲስተም) ጥቅም ላይ አለማዋል ሀብትን በቁጠባ እንዳይጠቀሙ እና የግዥ ሥርዓቱም በእቅድ እንዳይመራ ስለሚያደርግ፣ የግዥ ስርዓቱን ለሙስና ስጋት እንዲጋለጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በ2014 የበጀት ዓመት የግዥ ሪፖርት መሰረት ሁሉም በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች አለመኖራቸው ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ የመንግስት ተግባራት አንዱ ግዥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ያለ እቅድ እና ቁጥቁጥ ላይ የተመሰረቱ ግዥዎች የሚዘወተር መሆኑን ነው፡፡ ያለእቅድ የሚፈፀሙ ግዥዎች በሥራ ክፍሎች ፍላጎት ላይ የመመስረት እደሉ አነስተኛ ከመሆኑ ባሻገር ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ የሚካሄድ አለመሆኑ አላስፈላጊ እቃዎች እንዲገዙ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ያለ ዕቅድ የሚገዙ ግዥዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ መሆኑ ሲታይ ሂደቱ ለሀብት ብክነት የሚኖረው አስተዋፅኦ ክፍተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው በተቋማት የሚፈፀሙ ግዥዎች በገበያ ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸው በምልክታ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለይ ግዢዎች በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ካልሆኑ በተጋነነ ዋጋ ላይ ተመስርተው እንዲፈፀሙ ሊደረጉ መቻላቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ ግዥ የሚፈፀምበት ሁኔታ መኖሩ ከፍተኛ የመንግስት መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት የስራ ዘርፍ ህጋዊ አሰራርና ስርዓትን ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ ለሙስና እና

ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል፡፡ እንዲሁም ለጥቅም ግጭት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

- የግዢ ስርዓቱን ከሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል አስተዋፅኦ የሚኖረውን ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ስርዓትን ሁሉም ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ ተግባረዊ እየተደረገ አለመሆኑ ምልከታው ያሳያል፡፡ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉም ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ኤሌክትሮኒክ ግዥ ግልፅነት ለማስፈን ካለው ጥቅም ባሻገር ተጠያቂነት በሚያስከትል መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል ተገቢ ትኩረት ያሻዋል፡፡

3.7. የሰው ሀብት አስተዳደር

በዘርፉ ውስጥ ያሉት ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን ኮሚቴ በማቋቋም ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ በዘርፉ ስር ባሉት ተቋማት 36 ቅሬታዎች ቀርበው 36ቱም ውሳኔ ማግኘታቸውን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 100% ይሆናል፡፡ ከዚህም በመነሳት በዘርፉ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ የመስጠት ስራ መሰራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሰራተኛ ቅጥር ለመፈፀም ተቋማቱ ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሀን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆንም ለማደረግ የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋ መሆኑና ሕጉን በተከተለ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

የትምህርት ማስረጃ እና ስራ ልምድ የማጣራት ስራ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ስለመከናወኑ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ የአመራር ሹመትና የሰራተኞች ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተቋማቱ ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት የማደራጀት ጅምር ስራ ቢኖርም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በሚ/ር መ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማጎልበቻ (41 አመራርና 120 ሰራተኞች) እና የሥነ-ምግባር ማሻሻያ (28 አመራርና 309 ሰራተኞች) ስልጠናን መስጠቱን የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳይ ሲሆን በሶስት ተቋማት ግን ስልጠና ስለመሰጠቱ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- የሰራተኛው ማህደር የማጥራት ስራ ሙስናን ለመከላከል አንዱ መሳሪያ ሆነ ሊያገለገል ይችላል፡፡ የማጥራት ስራው በዋናነት የሚካሄደው ድግሞ የትምህርት ማስረጃ እና ስራ ልምድ የማረጋገጥ ስራ ሲሰራ ነው፡፡ ሆኖም በጥናቱ የተካተቱት የዘርፉ ተቋማት ማስረጃወችን የማረጋገጥ ስራ አለመስራታቸው ነው፡፡ ይህ አላግባብ የውሸት ሰነዶች ላይ ተመስርቶ ለሚፈፀም ሙሰና ስጋት ተቋማቱን ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡
- ስልጠና ሙሰናን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ተጋባራዊ ማደረግ ላይ ወስንነት እንዳለ ከምልከታው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ተቋማቱ የሰራተኛውን ስነምግባር በማሻሻል በኩል አስተወፅኦ ሊኖራቸው የሚችሉ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት የአመለካካት ለውጥ ለማምጣት የሚያደርጉት ጥረት ደካማ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ የአመለካካት ለውጥ ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ለቅደመ መከላከል ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት አስተዳደር አለመገንባቱ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ስለሚያስከትል፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

3.8. የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ህግ በሚደነግገው መሰረት የፈደራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ሀብታቸውን የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተቋማትም ቅጥር ከመፈፀማቸው በፊት የመጀመሪያ ወይም ዳግም ምዝገባ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት በዘርፉ ስር ያሉ በሁሉም ተቋማት ውስጥ የሀብት ምዝገባ ማድረግ ከሚገባቸው 41 አመራሮች ውስጥ 22፣ እንዲሁም ከ2,999 ሰራተኞች ውስጥ 778 ብቻ ሀብታቸውን እንዳሳወቁ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የምዝገባ ሂደቱ በተጠናከረ መልኩ ማካሄድ የሁሉም ሰራተኞች ሃላፊነት ቢሆንም

የተቋማት አመራርም የምዝገባ ሂደቱ ቀልጣፋ እንዲሆን ስራ መስራት ይጠበቅበታል። ውጤታማ ምዝገባ ማካሄድ ምንጩ ያለታወቀ ንብረትና ገንዘብ ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን በመገንዘብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

3.9. ኦዲትና ቁጥጥር

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ባግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ የውጭ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው። በዘርፉ ዉስጥ ባሉ ተቋማት ያለው አሰራር እንደሚከተለው ተተንትኗል። በዘርፉ ያሉ ተቋማት በየዓመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን ከሪፖርቶች መገንዘብ ይቻላል። በየተቋማቱ ያሉ አመራሮች የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የሚያካሄዱ መሆኑን ለማዎቅ ተችሏል። በ2014 በጀት አመትም የውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ አብዛኛው ተቋማ ውይይትና ግምገማ ያካሄዱ መሆኑን የግምገማ ቃለ-ጉባኤዎች ያስረዳሉ።

2014 በጀት አመት የውጭ ኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ ይህ መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት ተጠናቆ የቀረበ ኦዲት ሪፖርት ግኝቱን በዝርዝር ቀርቦ ለማየት አልተቻለም። የውስጥ ኦዲት በየሩብ አመቱ ይከናወናል። የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ዉስጥ ያሉ ሁሉም ተቋማት በትብብር ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ከኦዲት ተደራጊው የሥራ ክፍል በስተቀር ለሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆንበት አሰራርና ልምድ አለመኖሩን ከተጻፉ ደብዳቤዎች ለማየት ተችሏል።

የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ከማሻሻል አንፃር የፋይናንስ መረጃ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS - Integration Finance Information System) እንደሚጠቀሙ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ቢሆን በ2014 በጀት ዓመት የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝት እንደሚያሳዬው በዘርፉ ባሉ 4ቱም ተቋማት ያለው ያልተወራረደ (ተሰብሳቢ ገንዘብ) በአጠቃላይ 30,442,923.64 ብር በግኝት የተመዘገበ ሲሆን፣ እንዲሁም የፕላንና

ልማት ሚ/ር መ/ቤት ሰራተኞች ላልሆኑ የውሎ አበል ክፍያ ከፍሎ መገኘቱ እና የሥልጠና ተሳታፊ ተብሎ ስልጠናው የተሰጠበትን፣ የተፈቀደበትንና ስልጠናውን ስለመካፈላቸው የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር የተከፈለ ገንዘብ ስለመኖሩ ከውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፡-

- የኦዲትና ቁጥጥር ስርዓት የመንግስትን ሀብት ከብክነት ለመታደግ፤ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመከላከል ያለው ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዋናነት አመራሩ በኦዲት ግኝት ተመስርቶ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ግኝት ላይ ተመስርተው የተወሰዱ እርምጃዎች የሚሳይ መረጃ በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት ማግኘት አልተቻለም፡፡ የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ መሆናቸው የሚያሳይ መረጃም አልቀረበም፡፡ ሪፖርቶች ተደራሽ አለመሆናቸው አመራሩ አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት ያለው ተነሳሽነት ውስን መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ይህም በተቋም ውስጥ ተጠያቂነት ለማሰፍን የሚሰራው ስራ ውጤታማ እንዳይሆን ሊያደርገው ስለሚችል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- የኦዲት ሪፖርት በተመለከተም ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት በተለይም ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ ለህግ ፣ለተቋማዊ ለዉጥና የመገናኛ ብዙሃን በተደራጀ መልኩ ተደራሽ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ይህም የሙስና ስጋቶች በጋራ በመየት የተቀናጀ ስልትና ፖሊሲ በመንደፍ በተቋም ደረጃ ሙስናን የመከላከል ስራ ለመከወን አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አንጻር ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ከዘርፉ ተቋማት አመራሮች ይጠበቃል፡፡

3.10. የሙስና ስጋት ጥናት

ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ስጋት የሆኑ የስራ ሂደቶችን ዝርዝር፣ የመከሰት እድልን እና ተጸዕኖን (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ) ከታች በሰንጠረዡ ተዘርዝሯል፡፡

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች	የመከሰት ዕድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተጽዕኖ	የስጋቱ መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
1	ፋይናንስ	መካከለኛ	ከፍተኛ	የሰው ኃይል እጥረት፣	የሰው ኃይል ማሟላት፣ ጸም
2	ግዥ አፈጻጸም	መካከለኛ	ከፍተኛ	➢ የቁጥ ቁጥ ግዥ ስለሚፈፀም ➢ የክትትልና ቁጥጥር ማነስ	➢ ግዥን በእቅድ መፈጸም ➢ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር
3	ንብረት አስተዳደር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ የሰው ኃይል እጥረት፣ ቅጥር በመከልከሉ ምክንያት ➢ ተሽከርካሪን ጨምሮ ከፍተኛ ንብረት እለሚያንቀሳቅስ ና የቁጥጥር ስርአቱ ደካማ በመሆኑ	➢ ከሲቪል ሰርቪስ በማፈቀድ ቅጥር መፈፀም ➢ ጠንካራ የቁጥጥር ስርአት መዘርጋት
4	አይ.ሲ.ቲ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ ቴክኒካል ጉዳይ በመሆኑ ለቁጥጥር አለመመችት (ለኦዲት)	➢ ኦዲተሮች የአይ.ሲ.ቲ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ
5	አይ.ኤስ.ቲ (IST)	ከፍተኛ	ከፍተኛ	➢ ተቋሙ የመረጃ ተቋም ስለሆነ ብዙ ሰርቨሮችን እና አፕሊኬሽኖችን ስለሚገዛና እስፔስፊኬሽ እና TOR ተመሳሳይ ሰው ስለሚያዘጋጅ ከፍተኛ ተጋላጭነት አለው	➢ የሚዘጋጀው እስፔስፊኬሽ እና TOR በተለያዩ ሰወች እንዲዘጋጅ ማድረግ

ምዕራፍ አራት

መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳቦች

4.1. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የነበረው፣ በፕላንና ልማት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመዳሰስ የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አቢይ ዓላማ ስር በጥናቱ መቋጫ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡ አምስት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፡- 1ኛ. የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣ 2ኛ. የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ እና 3ኛ. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በሪፖርቱ ላይ ከቀረቡትን አበይት የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግየሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

1. በዘርፉ ያሉት የስነምግባር ክፍሎች በሰው ሃይል እና በተለያዩ ግብአቶች የተሟሉ መሆናቸው ተቋማት በአዋጅ የተጣለባቸወን ሃላፊነት ለመወጣት ጥረት ማድረጋቸው ያሳያል፡፡ ሀኖም ስነምግባር ክፍሉ የበጀት ነፃነት ያለው አይመስልም፡፡ ይህ አቅዶ ስራው እንዳይሰራ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተደራጀ መልኩ ለመዋጋት የሚያስችል ቅንጅታዊ ስራ እየተሰራ አመሆኑን ታይቷል፡፡
2. በሙስና ስጋት ዙርያ እና በተገልጋዮች እርከታ ላይ ጥልቀት ያላቸው ጥናት የማካሄድ ልምድ አለመዳበሩ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ተጠያቂነት ስራ እየተሰራ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
3. እስከ ታችኛው የተቋም ክፍሎች መረጃ ተደራሽነት ስራ አጠጥጋቢ በሚባል ደረጃ አለመሆኑን ለማስተዋል ተችሏል፡፡ የእቅድና አፈፃፀም መረጃዎችና ሪፖርቶች በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ አከባቢ ላይ ተንጠልጥሎ የመቅረት አዝማሚ መኖሩን ይታያል፡፡ ፡
4. በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ዙርያ ለአስፈፃሚው አካል ስለጠና የመስጠት ልምዱ የለም በሚባል ደረጃ ላይ መሆኑን ነው፡፡
5. በተቋማቱ ያለው የንብረት አስተዳደር ለማዘመን የሚያስችሉ የካይዘን ስርኣት እና የአውተሜሽን ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተስተውሏል፡፡
6. በዘርፉ ተቋማት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ተስተውሏል፡፡

7. በዘርፉ ባሉ ተቋማት የአስፈፃሚው ስነምግባር ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ስለጠናዎች አየተሰጠ አመሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡
8. ሃብት በማሳወቅና ማስመዝገብ ስራ ዙሪያ የተሰራው ስራ ትልቅ ስኬት ማሳያነው፡፡ ይህም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መረዳት ተገቢ ነው፡፡
9. የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ አለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮች እና ሙሰናን ለመዋጋት የሚስችል ሁኔታ አለመፈጠሩ ነው፡፡

4.2. የመፍትሄ ምክረሃሳቦች

ከላይ ከቀረበው ትንታኔ እና ድምዳሜ አኳያ የሚከተሉት ምክረሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

- የስነምግባር ክፊሎች ስራቸውን በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የበጅት ነፃነት እንዲኖራቸው ቢደረግ የተሻለ ስራ እንዲሰሩ ሊያግዛቸው ይችላል፡፡
- መስናን የመዋጋት ስራ የተቋም አመራር ሃፊነት መሆኑን በመገንዘብ አመራሩ የስነምግባር ግንባታው እና የመከላከል ተግባር በተደረጃ እና በተጠናከረ መልኩ ሊመራው ይገባል፡፡
- ሙስናንና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት ፋይዳ ያላቸው የስራ ክፍሎችን በቅንጅት የሚሰሩበት ስራ የማመቻቸት ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ስለሆነም የተቋማት ኃላፊዎች፣ የህግ፣ የለውጥ፣ የውስጥ ኦዲትና የስነመግባር መከታያ ክፍሎችን አቀናጅቶ መጠቀም የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጉና አፈጻጸማቸውንም ሊገመግሙ ይገባል፡፡
- የሙስና ስጋት እና የተገልጋዮች ጥናት በማካሄድ ችግሮችን ለይቶ ተጠያቂነት የማስፈን ስራም ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡
- የንብረት አስተዳደሩ እና የግዥ ስራአቱ በአውቶሜሽን የማዘመን ሰራ ተግባራዊ ማድረግ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡
- የመረጃ አያያዝ እና ስርጭት ላይ ግልፅነት በሚያሰፍን መልኩ የማዘመን ሰራ መስራት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- ሃብት የማሳወቅ እና ምዝገባ ስራውም በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ማደረግ ያለው አፈፃፀም ቀጣይነት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡

- የሰው ሃብት አቅም ግንባታ ስራ በተጨማሪም የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስኛዎች ማጥራት በትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡
- የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የማድረግ ስራ መሰራት አለበት፡፡